# መደመር ለሃገራዊ መግባባት መተካት ኣይችልም

ኣባዲ ኣባይ abadiabay4@gmail.com

ኢህኣደግ እያካሄደው ባለው በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ በሃገራችን ኣዲስ ክስተት እየተፈጠረ ይገኛል። ኢህኣደግ በጀመረው የመታደስ እንቅስቃሴ እየታደሰ ነው ወይስ እየተቀየረ የሚለው በጣም ኣከራካሪ ጉዳይ እየሆነ ይገኛል። ይህንን ዓብዩ ጉዳይ ለግዜው ትተን ኣዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ያነሱት መደመር የሚል መፎክር እና ሃገራዊ መግባባት መፍጠር የሚለው ኣቅጣጫ ኣነፃፅረን ብናያቸው ጠቃሚ ይመስለኛል። ሃገራዊ መግባባት መፍጠር ማለት በዋና ዋና ሃገራዊ ኣጀንዳዎች ኣብዛኛው ህዝብ የጋራ መግባባት መፍጠር  ማለት እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልፀዋል። ኣንኳር ሃገራዊ ኣጀንዳዎች የሚባሉት፡- ድህነት ቁጥር ኣንድ ጠላታችን መሆኑ፣ ኢትዮጵያ የብዙ ህዝቦች ኣገርና ለሁሉም ህዝቦች በእኩልነት የምታስተናግድ ሃገር መሆን እንዳለባት፣ ህግ እና ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ማክበርና ማስከበር፤ የምንገነባው ነፃ የገበያ ስርዓት ፌደራላዊ ኣወቃቀር የተከተለና በልማታዊ መንግስት ኣቅጣጫ መሆን ኣለበት በሚሉ ጉዳዮች የጋራ ግንዛቤና ኣረዳድ መፍጠር ያካትታል። ይህ እሳቤና ኣቅጣጫ የምእራባውያን ከሚከተሉ Political Hegemony የመፍጠር እስትራቴጂና የሩቅ ምስራቅ ኣገሮች ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ከተከተሉት Sense of Urgency ተመክሮ በመውሰድ የተቀመረ ሃሳብ ነው።

መደመር የሚለው ሃሳብ የኢትዮጵያ ሃገራዊ ማንነት፣ ፍቅር ያሸንፋል በሚል መፎክርና የደቡብ ኣፍርካ ሞዴል የመሰለ የይቅርታና እርቅ ኣገባብ መከተል የሚል ይመስለኛል ጠቅላይ ሚኒስተሩ ከሚገልፁት እንደገባኝ። ከኣዲሱ መሪያችን መደመር የሚል መፎክር በማንሳት ሃገራዊ ማንነት የገነባ ሃገር ወይም የተቀነባበረ ፖለቲካዊ ፅንስ-ሓሳብ ማግኘት ኣልቻልኩም። መደመር የሚል ሃሳብ ለሃገራችን ኣዲስ ኣይደለም። ወደድን ጠላንም ሃፀይ ሚኒሊክ ደምረውን ነበር። ሃፀይ ሃ/ስላሴ ጣልያን የወሰዳት ኤርትራ መልሰው ደምረውን ነበር። ኮ/ር መንግስቱ ኣንዴ ስለጥንታዊት ኢትዮጵያ ሌላ ግዜ ስለ ህ/ሰባዊት ኢትዮጵያ እያነሳ ስለኣንድነት ብዙ ሰብኮናል። ይህን ለኣንድ መቶ ዓመታት የቀጠለ የመደመር ኣካሄድ ኣንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማሕበረሰብ ኣልፈጠርም። ተደምረን ምን ይዘን እንደምንጓዝ፣ በየትኛው ኣቅጣጫ በጋራ እንደምንፈስ፣ መድረሻችን የት መሆኑ መግባባት ስላልነበረ ነው ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር ወደ መፍረስ ተቃርባ የነበረችው። በመሆኑ ለብሄራዊ መግባባት የሚለው ኣምር መደመር እና ፍቅር የሚለው ሃሳብ ከተውንም ሊተካው ኣይችልም። ቀጥለን ኣሁን በተረ-ስልጣን

የጨበጠው ሃይል በመደመር ይሁን በማፍቀር የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጭው ብለን ብንጓዝ እኳ የምንመኘው ሰላም፣ አንድነትና እድገትን ማስቀጠል እና ማስመዝገብ ይችላል ወይ የሚለው እንመልከት።

<u>አሁን በየአደባባዩ ምስላቸው የምናያቸው ግለሰቦች የሃሳብና የተግባር አንድነት የላቸውም</u>

የኦህዴድ ዝቅጠት የወለደው አዲሱ ሃይል ቄሮ አደራጅቶ ወደ አመፅ በማስገባት ስልጣን የኦሮሞ ተወላጅ እስካልያዘ ደረስ ሰላም በዚህ ኣገር ኣይኖርም ብሎ በአመፅና በተጠላለፈ ኔትዎርክ ወደ ስልጣን የመጣ ሃይል ነው። የኦሮሞ ወጣቶች ጉልበታቸውና እውቀታቸው ኣጣምረው የክልሉ መሬትና የተፈጥሮ ሃፍት ተጠቅመው ሃብት እንደፈጠሩ እያስረዳና እያስተማረ ሳይሆን በውጭ ይሁን በሃገር ውስጥ ባለሃብቶች የተቋቋሙት ተቋማት እንደሚያካፈላቸው ቃል እየገባ ስልጣን ለመያዝ የበቃ ሃይል ነው።ይህ በመሆኑ ኣዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ከተመረጡ በሁለተኛ ወር ለኦሮሞ ጥቅም ኣልሰራህም ተብለው በኣድማ በተካሄደው ኮንፈረንስ ባልተጠየቁ ነበር። እሳቸው ቢሆኑ ለሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች ለመጥቀም ነው የተመረጥኩት ኣላሉም። በዚህ ኣጭር ግዜ በሃገር ውስጥና በውጭ ያስፈታሁዋቸው እስረኞች ኣብዛኞቹ ኦሮሞ ናቸው ለኦሮሞ በልዩ ትኩረት እየሰራሁ ነኝ እናንተ ግን ኣልገባቹም ብለው መልስ ባልሰጡ ነበር።

በሌላ በኩል በኢህኣደግ ድርጅቶች ያለው እኩል ውክልና በህዝብ ብዛት እንደሚቀየር ከዓፋር ሽማግሌዎች ባደረጉት ወይይት ኣንፀባርቀዋል። በኣጠቃላይ የኦሮሞ ህዝብ ብዛት ስላለው ሃገሪቱ የመምራትና ቀጣይ እጣ ፋንታ መወሰን ኣለበት የሚልና የኦሮሞ ቋንቋ በሌሎች ብሄሮች ለመጫን ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ኣክራሪ ብሄራዊ ሃይል ነው። ይህ ሃይል ህዝብ እንደህዝብ በእኩል ኣይን የማየት ችሎታ የሌለው በመሆኑ መደመር የሚለው ሃሳብ በራሱ ደካማ ቢሆንም ሊደምረን ሊያፈቅረን የሚችልበት የሃሳብና የሞራል ዓቅም የለውም።

በብኣዴን የመስመር ዝንፈትና ዝቅጠት ምክንያት የተፈጠረው ሃይል ቢሆንም ለእኩልነት ደንታ የሌለው የኣማራ ገዢ መደብ ኣስተሳሰብ ለማስመለስ የሚጥር ሃይል ነው። ሰነ/24/2010 ዓ/ም በባህርዳር በተካሄደው ሰልፍ የክልሉ መሪ የድሮ የኣማራ ገናናነት እናስመልሳለን ብለዋል። የኢትዮጵያ ህዝቦች የነበራቸው የቀድሞ ገናናነት ለማለት ሞራል ኣልነበራቸውም። በአንድ በኩል በሃገራችን የብሄር ጭቆና ኣልነበረም፣ የነፍጠኛ ስርዓት የሚባለው የኣማራ ህዝብ ሞራል ለመንካተ የተፈጠረ ስሁት ድምዳሜ ይላሉ። ይህንን መፎክራቸው ለማሳካት የኢትዮጵያ ኣንድነት ለማስጠበቅ መጀመርያ የኣማራ ክልል ማስፋት በሚልና ኣዲስ የመደመር ዘዴ ኣስመስለው የትግራይ፣ የዓፋር፣ የቤንሻንጉልና ከፊል የኢጋራቸው የኦሮሚያ ክልል

የሚያጠፋና የሚነካ ኣዲስ ካርታ ኣሰርተው በመንቀሳቀስ ይገኛሉ። ህውሓት እንደ ድርጅት እየኮነነ የደርግ ፋሽሽታዊ ስርዓትና የስነ-ሃሳብ መሪው የነበረው የመኤሶን መሪዎች ሲያሞግሱ ኣይተናል። ከዚህ ኣልፎ ፍፁም የብሄር እኩልነት የማያምኑትና ኢትዮጵያ እንድትበታተን ሲሰሩ ለነበሩና ኣሁንም እየሰሩ ላሉት የኤሬትራ ፕሬዝዳንት የሚያመሰግን ሃይል በማሰባሰብ እንደመር እያሉን ነው።

ኣሁን የወጣቱ መንፈስ የቀለም ኣብዮት በሚመስሉ መፎክሮችእያንቀሳቀሰ ያለው ሃይል 1997 ዓ/ም ቅንጅት የሚባለው ሃይል ፈጥሮት የነበረው መንፈስ በመፍጠር ሃገር ማፍረስ ካልሆነ በስተቀር ኣዲስ የተሃድሶ እንቅስቃሴ የሚመራበት በጋራ የሚያምንበት Synergy Create የሚያደርግበት Collective Decision and Shared Knowledge የለውም። ሃገሪትዋ የምትደመርበት ሂደትም ቢሆን Synergy Creation Process ላይ የጋራ ግንዛቤ የለም። ከብኣዴን የፈለቀው የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም  እየጠየቀ ነው። የኦህዴድ ደግሞ የኢህኣደግ ድርጅቶች በኔትዎርክና በማስፈራራት ወደ ራሱ በመዋጥ የበላይነቱ ቀጥሎ እንድሄድ እየፈለገ ነው። ሁለቱም ሃይሎች ለግዜው በመውጫ የተጣበቁ ናቸው የሚባሉበት ምክንያት የጋራ ግብን ራእይ ስሌላቸው ነው። የተቀመረ ኣዲስ ሃሳብ፣ የምትጓዝበት ኣቅጣጫ እና የምትሄድበት መድረሻ ሳታውቅ መደመርም ይሁን መፋቀር የኣውድ-ምህረት ስብከት እንጂ ተጨባጭ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የማምጣት ችሎታ የሌለው ግዚያዊ ስሜት የሚገዛ ወሬ ነው የሚሆነው።

<u>ኣዲሱ ሃይል የሃገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የጨመረበት ኣቅሙ ምን ይመሰላል?</u>

የሃገራችን ኢኮኖሚ ግብርና መር መሆኑ ይታወቃል። የኢኮኖሚ እድገቱ የሚወስነው እያንዳንዱ ኣርሶ ኣደር እና ኣርብቶ ኣደር ምርታማነቱ ሲጨምር መሆኑ ይታወቃል። ኣሁን ያለው ኣመራር በያንዳንዱ ማሳና ስድራ ቤት ገብቶ ኣርሶ ኣደርን መደገፍ እንደዋነኛ የስራ ሃላፊነቱ መሆኑ የተገነዘበ ሃይል ኣይመስለኝም። ሌላ ቀርቶ የእድገትና ትራንስፎርመሽን እቅድ በኣግባቡ ተገንዝቦ ግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ከመሸጋገሩ በፊት ግብርና በኣመራረትና ምርታማነቱ መጀመርያ ትራንስፎርም መሆን እንዳለበት የተገነዘበ ኣመራር እየሰጠ ኣይደለም። ጠቅላይ ሚኒስተራችን ለወጣቶች እንዴት በቤቴክርስትያን እና በትምህርት ቤት ኣከባቢ ያለው ኣጥር ማስዋብ እና ችግኝ መትከል እንደሚችሉ እየመከሩ ኣርሶ ኣደሩን እንዴት መደገፍ እንዳለባቸው ያሉት ነገር የለም።

በሌላ በኩል ኣሁን ያለው የኢኮኖሚ ችግር ለመፍታት የማይክሮ ኢኮኖሚ ቫርዮሽልስ ተረድቶ እና በልማታዊ መንገድ እንዴት እንደሚያረጋጋው እስካሁን ያለው ነገር የለም። የዋጋ ግሽበት

እየጨመረ ነው፣ ስራ ኣጥነት እየሰፋ ይገኛል፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እየተንሰራፋ ይገኛል። በኣጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እድገቱ እየተገታ ይገኛል። ይህን ችግር የልማት ሓይሎች በኣግባቡ በማሰማራት ከመፍታት ይልቅ ኣንዴ መልመና እና ድጋፍ፣ ሌላ ግዜ ኣሁን በእጁ ያሉት ተቋማት በመሸጥ ወይም ድፍድፍ ነዳጅ በመሸጥ ግዚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ብቻ እየሰራ ይገኛል። በኣጠቃላይ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ኣርሶ ኣደሮች በኣግባቡ በማሰማራት፣ የግል ባለሃብቱ ኣቅጣጫ በማስያዝና የመንግስት መሪ ሚና በኣግባቡ ተረድቶ ኢኮኖሚው የመምራት ችሎታና ሞራል ኣላየሁበትም። የሚበላ ነገር የሌለው መደመርና ፍቅር በኣሸዋ ላይ ስለሚመሰረት ዘላቂነት የለውም ብቻ ሳይሆን የኣንዱን ማጣት ሌላው መጥቶ በመስራቱ እየመሰለው እርሰ በርሱ የሚገፋፋበት ሁኔታ ይቀጥላል። በድህነት ኣረቋ ውስጥ ለኣንድ ዳቦ ለማግኘት ሌላው መግፋት ከመጣ መደመር፣ ፍቅር፣ እና ኣንድነት የውሃ ሽታ ይሆናል።

በኣጠቃላይ የኣሁን ያለው ኣመራር የኢህኣዴግ ብልሽት የወለደው በመሆኑ ውልደቱ እና እድገቱ የተዛባ ሓይል ነው። ይህንን ባህሪው ከዘላቂ ጥቅም ግዚያዊ ድሎችን እያጋነነ የማይደመሩ ለመደመር የሚታትር ፍጡር ሆነዋል። መገንጠልና ፍፁም ኣንድነት የሚሉ ኣምር ለማፋቀር በሚል እሳቤ የተጀመረው የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና ኢኮኖሚያዊ እድገት እያፈረሰ እንደ ኣዲስ ለመጀመር እየጣረ ይገኛል። ይህንን ኣካሄድ ኣንድነት ከመፍጠር ይልቅ ሃገሪትዋ እንደሚበታትናት ኣውቀን በግዜው ሃይ ሊባል ይገባል።